# መብትዎን ይወቁ በሥራ ቦታ

ከሠራተኛ ደረጃዎች (መብት) ጽሕፈት ቤት (Office of Labor Standards) ጋር

አቅራቢ፦ ኮሊን ፎንታና፡-ከሠራተኛ ደረጃዎች (መብት) ጽሕፈት ቤት (OLS)

# እኛ ማን ነን?



ተልእኳችን በታቀደ የማህበረሰብ እና የንግድ ተሳትፎ ስልታዊ የህግ ማስከበር ስራን እና አዳዲስ የፖሊሲ ቀረጻዎችን በመጠቀም የሰራተኞችን መብትና ደረጃ ማሻሻል ሲሆን፣ ይህንንም ለዘር እና ለማህበራዊ ፍትህ ባለን ቁርጠኝነት እናከናውናለን።

# የምንሰራቸው ሥራዎች

- ምርመራዎች
- የማህበረሰብ ተደራሽነት እና ትምህርት
- እገዛ እና ስልጠና
- ግብዓቶች እና መረጃዎች

Seattle Office of Labor Standards


# አጀንዳ



- መግቢያ እና የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት
- ዝቅተኛ ክፍያ (ደመወዝ) እና የክፍያ (ደመወዝ) ስርቆት
- የቤት ሠራተኞች ጥበቃ
- መተግበሪያዎችን/አፕሊኬሽንን (App) በመጠቀም ሥራ ለሚሠሩ ሠራተኞች የሚደረጉ ጥበቃዎች
- በህመም እና በደህንነት ምክንያት የሚከፈል የእረፍት ጊዜ
- ከበቀል እርምጃ (ከአድልዎ) የሚደረግ ጥበቃ
- መብቶቼ ካልተከበሩ ምን ማድረግ እችላለሁ?

Seattle Office of Labor Standards

# አስፈላጊ ማስታወሻዎች (ነጥቦች)



- **የኢሚግሬሽን (የስደተኝነት) ሁኔታዎ ምንም ይሁን ምን፣** ሁሉም የስራ ላይ መብቶችዎ በእኩልነት ይተገበራሉ



- የሰራተኛ ደረጃዎች ጽሕፈት ቤትን (OLS) በሚያገኙበት ወይም አቤቱታ በሚያስገቡበት ጊዜ፣ ጽሕፈት ቤቱ **የኢሚግሬሽን (የስደተኝነት) ሁኔታዎን በፍጹም አይጠይቅም**





- **ለሰሩት ስራ ክፍያ የተፈጸመልዎት በጥሬ ገንዘብ (ካሽ) ቢሆንም እንኳ፣** እነዚህ ሁሉ ጥበቃዎች ይደረጉልዎታል!

# ዝቅተኛ ክፍያ (ደመወዝ)



Seattle Office of Labor Standards

## በ2026 በሲያትል ዝቅተኛው የደመወዝ ክፍያ ተመን (Minimum Wage) ምን ያህል ነው?

# ዝቅተኛ ክፍያ (ደመወዝ)



## የ2026 የሲያትል ዝቅተኛ የደመወዝ ክፍያ በሰዓት $21.30 ነው

በዚህ የሰራተኞች መብት ጥበቃ የሚካተተው ማን ነው?

- አብዛኛው ሰራተኛ ዝቅተኛውን የደመወዝ ክፍያ (Minimum Wage) የማግኘት ህጋዊ መብት አለው!
- አንድ ሰራተኛ ብቻ ያላቸው የስራ ቦታዎችም ቢሆኑም እንኳ

- **ቢያንስ** ዝቅተኛውን የደመወዝ ክፍያ (Minimum Wage) የማግኘት መብት አለዎት
- ቃል የተገባልዎትን (የተመደበልዎትን) ሙሉ ደመወዝ የማግኘት መብት አለዎት

Seattle Office of Labor Standards

# የደመወዝ ስርቆት



## የደመወዝ ስርቆት ምንድን ነው?

Seattle Office of Labor Standards

# የደመወዝ ስርቆት



የደመወዝ ስርቆት ማለት ለሰሩበት ስራ ክፍያ አለማግኘት ማለት ነው!

**የክፍያ (ደመወዝ) ስርቆት የተለመዱ ምሳሌዎች፡-**

- ከመደበኛ የስራ ሰዓት ውጬ ያለ ክፍያ መስራት ("off the clock")
- የደመወዝ ክፍያ መዘግየት ወይም ሙሉ በሙሉ አለመከፈል
- ትክክለኛ ያልሆነ (ከተወሰነው በታች የሆነ) ዝቅተኛ ደመወዝ ወይም ቃል የተገባልዎትን ያህል ደመወዝ አለመከፈል
- ያልተወሰዱ የምግብ እና የእረፍት ጊዜያት
- ትክክለኛ ያልሆነ የደንበኛ ጉርሻ (ቲፕ) ክፍያ
- ያልተከፈለበት የትርፍ ሰዓት (Overtime) ስራ

# የቤት ውስጥ ሰራተኞች ጥበቃዎች



የቤት ውስጥ ሰራተኞች በቤት ውስጥ እና በቤት ዙሪያ የሚሰሩ ናቸው፡-

- የቤት ጽዳት ሰራተኞች
- ሞግዚቶች
- አትክልተኞች
- ምግብ አብሳዮች
- የቤት አስተዳዳሪዎች

Seattle Office of Labor Standards

# የቤት ውስጥ ሰራተኞች ጥበቃዎች



የሚከተሉት መብቶች አሉዎት፡-

- በሲያትል ዝቅተኛው የደመወዝ ክፍያ
- የምግብ እና የእረፍት ጊዜያት
- ሰነዶችዎን ይያዙ (ይጠብቁ)
- ከአድልዎ (ከመገለል) የመጠበቅ መብት
- ተከታታይ ስድስት ቀናት ሲሰሩ የአንድ ሙሉ ቀን ዕረፍት (አብረው ለሚኖሩ/አዳሪ ሰራተኞች)

**Seattle** Office of Labor Standards

# የቤት ውስጥ ሰራተኞች ጥበቃዎች




አዲስ የክፍለ-ግዛት ሕግ!
የሚከተሉትን የማግኘት መብት፡-

- የጽሑፍ ስምምነት
- የስራ ስንብት ማስታወቂያ እና የስንብት ክፍያ
- የግላዊ መረጃ ጥበቃ መብቶች

Seattle Office of Labor Standards

# በመተግበሪያ (App)ላይ የተመሰረተ ሰራተኛ ጥበቃዎች

ማን ይሸፈናል?

- በዓለም አቀፍ ደረጃ መተግበሪያን (App) ተጠቅመው የሚሰሩ ቢያንስ 250 ሰራተኞች ባሉት እና በሕጉ በሚሸፈን የኔትወርክ ኩባንያ (Network Company) ውስጥ በሲያትል መተግበሪያን ተጠቅመው የሚሰሩ ሰራተኞች
- በሕጉ የሚሸፈን የኔትወርክ ኩባንያ (Network Company) ደንበኞችን በመተግበሪያ አማካኝነት ከሚሰሩ ሰራተኞች ጋር ለማገናኘት የኢንተርኔት መተግበሪያዎችን (Apps) ወይም ፕላትፎርሞችን የሚጠቀም ድርጅት ነው

ማን አይሸፈንም?

- የራይድሼር (Rideshare) አሽከርካሪዎች አይሸፈኑም (አይካተቱም)
- በመተግበሪያ አማካኝነት የሚሰሩ ሰራተኞች የራሳቸውን የክፍያ ተመን በሚወስኑባቸው እና/ወይም አስቀድመው የተያዙ (የተቀጠሩ) የክፍያ አቅርቦቶች ባሏቸው መተግበሪያዎች ላይ የሚሰሩ አይሸፈኑም (አይካተቱም)

Seattle Office of Labor Standards

# በመተግበሪያ ላይ የተመሰረተ ሰራተኛ ጥበቃዎች፡-

# የዝቅተኛ ክፍያ ድንጋጌ

የሚከተሉትን የማግኘት መብት፡-

1. ለወሰደው ጊዜ እና ለተጓዙት ማይሎች የሚከፈል ዝቅተኛ ክፍያ
2. የተለዋዋጭነት (Flexibility) ጥበቃ መብቶች
3. ስለ አቅርቦቶቹ (ስለቀረቡት የስራ እድሎች) ግልጽ መረጃ



Seattle Office of Labor Standards

# መተግበሪያዎችን (App) ተጠቅመው የሚሰሩ ሠራተኞች ጥበቃዎች፡-

# ስራን ማገድ / አካውንትን መዝጋት (Deactivation)

የሚከተሉትን የማግኘት መብት፡-

1. ስራ ስለማገድ/አካውንት ስለመዝጋት ፖሊሲ መረጃ ማሳወቂያ
2. የተጣለውን የስራ እገዳ (ወይም የአካውንት መዘጋት) መቃወም / ይግባኝ ማለት
3. ስራ ከመታገዱ (ወይም አካውንት ከመዘጋቱ) ከ14 ቀናት በፊት የሚሰጥ ማስታወቂያ (በጣም ከባድ የሆነ የባህሪ ወይም የስራ ሥነ-ምግባር ጉድለት ሲያጋጥም ካልሆነ በስተቀር)።

ቅሬታዎን/አቤቱታዎን ለእኛ ያቅርቡ!

Seattle Office of Labor Standards

# መተግበሪያዎችን (App)ተጠቅመው የሚሰሩ ሠራተኞች ጥበቃዎች፡-

# የሚከፈልበት የህመም እና የደህንነት እረፍት ጊዜ (PSST)

የሚከተሉትን የማግኘት መብት፡-

በእያንዳንዱ ሲያትል ውስጥ ለተሰሩ 30 ቀናት፣ የአንድ ቀን የሚከፈልበት የህመም እና የደህንነት እረፍት ጊዜ



# በህመም እና በደህንነት ምክንያት የሚከፈል የእረፍት ጊዜ



**በሆነ ወቅት ከስራ ቦታ በህመም ምክንያት የቀሩበትን ጊዜ ያስታውሱ – ምን ተፈጠረ?**

- እረፍት መውሰድ (ከስራ መቅረት) ችለው ነበር?
- ክፍያ ተከፍልዎት ነበር?
- የእርስዎን የስራ ፈረቃ (Shift) የሚተካ ሰው ማፈላለግ ነበረብዎት?
- አሰሪዎ እንደታመሙ የሚያሳይ ማስረጃ ጠይቆዎት ነበር?

Seattle Office of Labor Standards

# በህመም እና በደህንነት ምክንያት የሚከፈል የእረፍት ጊዜ



**በህመም እና በደህንነት ምክንያት የሚከፈል የእረፍት ጊዜ ማለት፡-**
**ለጤና ወይም ለደህንነት ምክንያቶች ጥቅም ላይ የሚውል የሚከፈልበት የእረፍት ጊዜ።**

- የስደተኝነት (የኢሚግሬሽን) ሁኔታዎ ምንም ይሁን ምን ይህ ጥበቃ ይደረግልዎታል።
- ሲያትል ውስጥ የሚሰሩ ሁሉም ሰራተኞች የሚከፈልበት የህመም እና የደህንነት እረፍት ጊዜ (Paid Sick and Safe Time) የማግኘት መብት አላቸው
- ይህ ጥበቃ ጊዜያዊ፣ በትርፍ ሰዓት (ፓርት-ታይም) ወይም በወቅታዊ ስራዎች ላይ የሚሰሩትንም ያጠቃልላል

Seattle Office of Labor Standards

በጥልቀት ስንመለከተው..

# የሚከፈልበት የህመም እረፍት ጊዜ (Paid Sick Time)




## የሚከፈልበት የእረፍት ጊዜ (Paid time off)

- ለራስዎ ወይም ለቤተሰብዎ አባል በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም በሌላ የጤና ምክንያት እንክብካቤ ለማድረግ
- ወደ ሐኪም ቀጠሮ ለመሄድ (ለቅድመ-መከላከል ህክምና)

Seattle Office of Labor Standards

# በጥልቀት ስንመለከተው..

# የሚከፈልበት የደህንነት እረፍት ጊዜ (Paid Safe Time)



**የሚከፈልበት የእረፍት ጊዜ (Paid time off)**

- ለደህንነት ችግሮች (የቤት ውስጥ ጥቃት፣ ጾታዊ ጥቃት፣ እና ክትትል/ማሳደድ)
- በደህንነት ችግር ምክንያት የልጅዎ ትምህርት ቤት ከተዘጋ
- ለኢሚግሬሽን ፍርድ ቤት (አዲስ የዋሽንግተን ግዛት ጥበቃ)

Seattle Office of Labor Standards

# የሚከፈልበት የደህንነት እረፍት ጊዜ (Paid Safe Time)



- አዲስ፦ ለኢሚግሬሽን ፍርድ ቤት የክስ ሂደት የሚከፈልበት የእረፍት ጊዜ
- በግዛት (ስቴት) አቀፍ ደረጃ የሚደረግ ጥበቃ

Seattle Office of Labor Standards

# ስንት ሰዓት አገኛለሁ?



አነስተኛ ኩባንያዎች (ከ250 ሰዎች ያነሱ የሰራተኛ ቁጥር ያላቸው) ለሰሩት እያንዳንዱ **40 ሰዓታት፣ የ1 ሰዓት** የሚከፈልበት የህመም እና የደህንነት እረፍት ጊዜ ያገኛሉ



ትላልቅ ኩባንያዎች (250 እና ከዚያ በላይ ሰዎች ያሏቸው) ለሰሩት እያንዳንዱ **30 ሰዓታት፣ የ1 ሰዓት** የሚከፈልበት የህመም እና የደህንነት እረፍት ጊዜ ያገኛሉ




# በህመም እና በደህንነት ምክንያት የሚከፈል የእረፍት ጊዜ



- ከሶስት ቀናት የሚከፈልበት የህመም እና የደህንነት እረፍት ጊዜ በኋላ ካልሆነ በቀር የሐኪም ማስታወሻ (ማስረጃ) ማቅረብ አይጠበቅብዎትም።

Seattle Office of Labor Standards

# በህመም እና በደህንነት ምክንያት የሚከፈል የእረፍት ጊዜ




- የሚከፈልበት የህመም እና የደህንነት እረፍት ጊዜ ለምን እንደወሰዱ ምክንያት ወይም ዝርዝር መረጃ የመስጠት ግዴታ የለብዎትም።

እንዲህ ማለት ይችላሉ፡-

  - የሚከፈልበት የህመም እና የደህንነት እረፍት ጊዜ (paid sick and safe time) ሰዓቶቼን መጠቀም እፈልጋለሁ።
  - ስለታመምኩኝ የእረፍት ጊዜ እፈልጋለሁ።


Seattle Office of Labor Standards

# በህመም እና በደህንነት ምክንያት የሚከፈል የእረፍት ጊዜ



- ሰራተኞች የሚከፈልበት የህመም እና የደህንነት እረፍት ጊዜያቸውን መጠቀም ከመጀመራቸው በፊት አሠሪዎች 90 ቀናት ሊጠብቁ ይችላሉ።
- ነገር ግን ሰራተኞች በስራ የመጀመሪያ ቀናቸው ጀምሮ ሰዓታትን ማከማቸት (ማግኘት) ይጀምራሉ።

# የበቀል እርምጃ መውሰድ በህግ የተከለከለ ነው!



በስራ ቦታ ስላሉት መብቶች በመናገርዎ ወይም በመጠየቅዎ አሠሪዎች በእርሰዎ ላይ አድልዎ ሊፈጽሙ ወይም ሊጠይቅዎ አይችሉም (ይህ በህግ የተከለከለ ነው)።


የበቀል እርምጃ (የማግለል ወይም የቅጣት) ምሳሌዎች፡-

- በስደት (ኢሚግሬሽን) ሁኔታዎ ላይ በመመስረት የሚሰነዘሩ ዛቻዎች
- ከስራ ማባረር፣ የስራ ደረጃን ዝቅ ማድረግ ወይም የስራ ሰዓትን መቀነስ
- አድልዎ (ማግለል)

# የሰራተኛ መብት ጸሕፈት ቤት (OLS)እንዴት ሊረዳዎት ይችላል?



- በሲያትል ከተማ ውስጥ የሚሰራ ስራ



- ችግሩ የተከሰተው ባለፉት 3 ዓመታት ውስጥ ነው
  - በፍጥነት ቢሆን ይመረጣል!
- ደመወዝዎ በጥሬ ገንዘብ (ካሽ) የሚከፈልዎት ቢሆን እንኳ፣ ስለ ክፍያዎችዎ ማስታወሻ ይያዙ፣ የሰሩበትን ሰዓት በቀን መቁጠሪያ (ካላንደር) ላይ ይመዝግቡ፣ እንዲሁም ሰነዶችን በጥንቃቄ ያስቀምጡ



- ሕጉ ከጎናችን ነው/ህጋዊ መብት አለን
  - ለአብነት ያህል፣ እኛ በስራ ቦታ ላይ የሚፈጸሙ አድልዎዎችን ወይም ትንኮሳዎችን የመመርመር ስልጣን የለንም፤ ነገር ግን እነዚህን ጉዳዮች ወደሚያጠናው የሲቪል መብቶች ቢሮ (Office for Civil Rights) ልናገናኝዎት እንችላለን!
- COEF እና BOEF አጋር ድርጅቶች

Seattle Office of Labor Standards

# ያግኙን!

https://laborinquiry.seattle.gov/worker-inquiry/

አቤቱታ/ቅሬታ ለማቅረብ ወይም ከጉዳይ መርማሪ ጋር ለመነጋገር በስልክ ይደውሉ

(206 ) 256 -5297

ተጨማሪ ሰነዶችን እና የተተረጎሙ መረጃዎችን ለማግኘት ድረ-ገጻችንን ይጎብኙ!